በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሴፕቴምበር 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከሴፕቴምበር 21-30 እና ከኦክቶበር 1-10 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ..... - 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች- 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ..... - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት..... - 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... - 4 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... - 6 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... - 7 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ..... - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 21-30, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... - 9 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 21-30, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ..... - 9 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ..... - 9 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30, 024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... - 10 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 10 -

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... - 11 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት የሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠርና መስፋፋት አተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በመጠናከራቸው በአብዛኛው የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ቀጥሎ ተስተውሏል። ከዚህ በተጨማሪም ዝናቡ ለረጅም ጊዜ ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ወደ ነበሩት ደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል።


ወቅታዊው ዝናብ በዋናነት በምዕራብ የሀገሪቱ አጋማሽ፣ በመካከለኛውና በምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ የነበረው ሲሆን፣ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተለይም ከአስሩ ቀን አጋማሽ በኋላ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ ላይ በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ጠንካራ የደመና ሽፋን ላይ በመነሳት ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአስሩ ቀናት የዝናብ ስርጭት እንደሚያሳየው ለበርካታ ቀናት ዝናቡ ከሰሜን የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ ቀንሶ ተስተውሏል። በዚህም መሰረት በአሁኑ ጊዜ እየታየ ያለው የዝናቡ መጠንና ስርጭት ከሰሜንና ሰሜን ምሥራቅ እየቀነሰ መምጣትና በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ቀስ በቀስ እየተስፋፋ መሄዱ የወቅቱ ዝናብ መደበኛውን ፈር የተከተለ መሆኑን ያመለክታል። ከላይ እንደተገለጸው የዝናቡ ሁኔታ በተስፋፋ መልኩ ቀጥሎ ከመታየቱም ሌላ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከባድ ያለ ዝናብ እንደጣለ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በኮምቦልቻ 31.2፣ በጂማ 37.5፣ በነቀምቴ 36.5፣ በአይራ 34.0፣ በአልጌ 48.2 እና 40.0፣ በአንገር ጉቲን 50.6 እና 39.4፣ በአርጆ 34.8 እና 34.6፣ በባቲ 78.0፣ በበደሌ 34.2 እና 33.8፣ በቡለን 33.1፣ በቻግኒ 60.4፣ በጨፋ 33.4፣ በፉኚዶ 49.8፣ በጋምቤላ 59.0፣ በጊምቢ 34.7፣ በካቺሴ 64.2፣ በማጂ 50.0፣ በማሻ 40.2፣ በመተማ 48.1፣ በቴፒ 29.7፣ በተርጫ 38.7 እንዲሁም በላንጌ 42.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት በ22 በተለያዩ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

78.0 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካካል በአልጌ፣ በአንገር ጉቲን፣ በባቲ፣ በቻግኒ፣ በፉኚዶ፣ በጋምቤላ፣ በካቺሴ፣ በማጂ፣ በማሻ እንዲሁም በመተማ ይጠቀሳሉ (ምስል 1)፡፡




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን እና ደቡብ ወሎ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ላይ ከ31-180 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከትግራይ የመካከለኛው፣ የምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአማራ ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ወሎ እና ዋግህምራ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ እና አውሲ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረናና ምስራቅ ቦረና፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልልጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን እንዲሁም ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የኤረር፣ ነጎብ፣ ጃረር የቆራሄ፣ የሸበል፣ የሊበንና እና የዳዋ ዞኖች ላይ ከ6-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን እና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ዞኖች፤ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ሲያገኙ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ መደበኛ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20 /2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ በሆኑት በተለይም በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም በመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ የነበረው እርጥበት ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እና የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከመሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የክረምት ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታው የጎላ ነበር። በሌላ በኩል ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ስፍራዎች እየተስፋፋ ያለው እርጥበት በአካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ ከመኖሩም በላይ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ጎን ነበረው። በአንፃሩ በተከታታይ እርጥበት እያገኙ ባሉ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛት ጋር ተያይዞ በሰብል ላይ የውሃ መተኛትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት አካባቢዎች ሰብሎች በጎርፍ የመወሰድ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ በተለይም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በዳውሮ ዞን ተርጫ ከተማ ከነበረዉ ከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ የደረሱ ሰብሎች በጎርፍ የመወሰድ፣ በእንሰሳት እና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳደረሰ የተሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 4)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ተከዜ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ ባሮ አኮቦና የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተለይም በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ እና አባይ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው አዋሽ እና ኦጋዴን እንዲሁም በጥቂት አፋር ደናክል ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም እርጥበታማ የአየር ሁኔታ ለገፀ ምድርና ከርሰ ምድር የውኃ ሃብት መጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ ከመኖሩም በላይ ወደ ግድቦችና የተለያዩ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባዉን የዉኃ ፍሰት በመጨመር የተሻለ ውኃ እንዲኖራቸው አስችሏል፡፡ በሌላ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በኩል በአብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል እና ጥቂት የታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ደረቅ የአየር ሁኔታ ላይ ነበሩ (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ እየተዳከሙ ስለሚመጡ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭትም ይቀንሳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚሆን ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በደቡብ እና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በመጪዎቹ የሴፕቴምበር ሶስተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በሰሜን



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ የሚሄድ ሲሆንና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡


በመጪዎቹ የሴፕቴምበር ሶስተኛዉ አሥር ቀናት በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ጋር ተያይዞ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ የሚሄድ ሲሆንና፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ምዕራብ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ የቀበና፣ የጠምባሮ እና የማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ እንዲሁም የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ፣ አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም በወለጋና በደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፤ ጋምቤላ እና ደቡብ ምዕራብ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ወሎ እና ዋህግምራ ዞኖች፤ ከትግራይ የማዕከላዊ፣ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን፣ ቆራሂ እና ዳዋ ዞኖች፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 21-30, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 21-30, 2024
የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የኦክቶብር የመጀመሪያው አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ፤ ደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 3)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30, 024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የሴፕቴምበር ሶስተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለግብርናው ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና የሚፈጥር ምቹ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የሚኖረው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ እንዲሁም ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለፍራፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎትን ለማሟላት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በሌላ በኩል የእርጥበት ሁኔታው በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን አካባቢዎች ላይ የሚስፋፋ ሲሆንና፣ ይህም ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በአንፃሩም በአንዳንድ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል እንዲሁም የሚጠበቀው እርጥበት በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስቀድሞ ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሶስተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ የእርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውኃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የመስኖም ሆነ የሀይል ማመንጫ ግድቦችን የውኃ መጠን ከፍ ስለሚያደርግ በመጪው የበጋ ደረቅ ወራት አሰተማማኝ የሀይል አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል። በአንጻሩ ግን ባላፉት የክረምት ወራት ከተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት ጋር ተያይዞ አሁናዊ የውሃ መጠናቸው በጣም በጨመረባቸው እንደ ተንዳሆ፣ ከሰም፤ ቆቃ፣ ርብ፣ ጣና በለስ እና ፊንጫ ግድቦች በሚገኙባቸው የታቸኛው የተፋሰስ ክፍሎች ላይ ከመጠን በላይ የግድብ መሙላት እንዳያስከትል የቅርብ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል መስከረም የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን እርጥበት በመጪው የበጋ ደረቅ ወራት ጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችል አግባብ መሰብሰብና ማከማቸት ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et